# ዜጋ




ዜጋ አንደኛ አመት ቁጥር ስምንት ሰኔ 1992



## •ደካማ ፖለቲካ ደካማ ፖሊሲ ደካማ ኢኮኖሚ

• «ሻዕቢያ ሊያንሰራራ እንዳይችል ሆኖ መመታት አለበት»

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ?

## •ጦርነቱ ገና ነው !







1993


?

# ስሞኑን ከማን ጋር?



# "...ሻዕቢያ ሊያንሰራራ እንዳይችል ሆኖ መመታት አለበት"

ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ



*ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የተወለዱት በ1950 ዓ.ም. በደብረዘይት ከተማ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው በአፄ ልብነ ድንግል እና ናዝሬት በአፄ ገላውዴዎስ ት/ቤት ተምረው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በንፋስ ስልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናኝቁ።*

*በ1966 ዓ.ም. 12ኛ ክፍል ደርሰው የነበር ቢሆንም በወቅቱ በነበረው ግርግርና በዕድገት በኅብረት ዘመቻ ምክንያት እስከ 1969 ዓ.ም. ድረስ ትምህርቱን አቋረጡት። በወሊጋ ጊምቢ ልዩ ስሟ ሃሮ ከምትባለው የዘመቻ ጣቢያቸው ዘመቻውን እናምንበትም በሚል ተመልሰው 1969 ዓ.ም. የ12ኛ ክፍል መልኘቂያ ፈተና ወስደው በማለፋቸው ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገቡ።*

*በትምህርቱም አልገፉበትም። ሦስት ወር ያህል እንደተማሩ በተነሣው ብጥብጥ ትምህርቱን ጥለው ወደ በረሃ ወረዱ። ስለዚያም ሁኔታም ሲናገሩ፤ "ከኢሕአፓ ጋር ለመታገል ወደ ሜዳ ከገባሁ በኋላ በኢሕአፓ አመራርና አካሄድ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች አነሣን። በዚህ መክንያትም 19 ልጆች ፅንፈኞች ተብለን ታሰርን። ሁለት ወር እንደቆየን በአመራሩ ስምንቱ ተገደሉ። በዚያን ወቅት ከሕወሀት ጋር ጦርነት ስለነበር የተቀረውን ይዘውን ወደ ኤርትራ ገቡ። ወደ 7 ወር ኤርትራ ከተቀመጥን በኋላ ከየቦታው ትግሉን ባለመስማማት ጥለው የሚወጡ ልጆች ተሰባስበን ጉዞ ወደ ሱዳን ሆነ።" በማለት ይገልጻሉ።*

*በሱዳን ሁለት ዓመት ከቆዩ በኋላ ነበር በ1980 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. ላይ ወደ አሜሪካ ያኙት። የተቋረጠውን ትምህርታቸውን በመኘጠል በ1983 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. የመጀመሪያ ድግሪያቸውን ከስቴት ዩኒቨርስቲ ኦፍ ኒውዮርክ አገኙ። ከዚያም ኒውዮርክ ውስጥ በሚገኘው ስኩል ኦፍ ሶሳል ሪሰርች ከሚባል ዩኒቨርሲቲ የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ተኘብለው በርክ የሚባል ዩኒቨርስቲ ውስጥ በረዳት ኘሮፌሰርነት ማዕረግ በሙሉ ጊዜ መምህርነት ተኘጥረው ማገልገል ጀመሩ።*

*በ1994 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. አገራቸውን ለማየት የሁለት ዓመት ዕረፍት በመውሰድ ከነቤተሰቦቻቸው እንደመጡ በዚያው ኘሩ። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ባለሙያዎች በኘሬዝዳንትነት ማህበርን ከመምራታቸው በተጨማሪ ሌሎች የግል ሥራዎቻቸውን ይሰራሉ። ሙሉ ጊዜያቸውን የኢትዮጵያ በቆሎ እርሻና ኢንዱስትሪ አክሲዮን ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ናቸው።*

*ከአ.አ. ቄራዎች ድርጅት ጋር በመተባበር የተከማቸውን ተረፈ ምርትና ኘንድ በማንሳት ማዳበሪያ ለመስራት የተቋቋመውንም ድርጅት በሥራ አስኪያጅነት ይመራሉ። ይኼው ድርጅትም የሙከራ ምርትም በቅርቡ ጀምሯል።*

*ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም በመምህርነትም ያለገግላሉ። ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ዩኒቨርሲቲው የሚከፍላቸውን ደመወዝ በየዓመቱ ጥሩ ወጤት ለሚያመጡ ኅበዝ የኢኮኖሚ ተማሪዎች ሽልማት አውለውታል። እንግዲህ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር እንተዋችሁ።*

__ዜጋ__:- የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ዋና ዓላማና የሠራውስ ምንድነው?

__ዶ/ር ብርሃኑ__:- የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ከተቋቋመ ዘጠኝ ዓመቱ ነው። አንዱ ዋና ዓላማው በተቻለ መጠን በሙያው የተሰማሩትን ሰዎች በጥናትም፣ ሙያን በተመለከቱ ጉዳዮችም ማገዝና የኢኮኖሚክስ ትምህርትና እውቀትን በሀገራችን ማስፋት፣ በኢኮኖሚክስ ዙሪያ ሰፋ ያሉ ምርምሮች ማድረግ ነው። እነኝህን ምርምሮች በአባላቱ መካከል ማበረታታት ሌላው ዓላማ ነው። በሦስተኛ ደረጃ የኢትዮጵያን ሕዝብ የኢኮኖሚ ዕድገት ማገዝ ነው።

ባለፉት አራት ዓመታት የማኅበሩ ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች የሚባሉት በዓመት አንድ ጊዜ ዓመታዊ የኢኮኖሚስቶች ጉባኤ በማካሄድ ጉባኤው ላይ ጥናታዊ ጽሁፎች ማዘጋጀት፣ ጥናታዊ ጽሁፎቹ ላይም ውይይት ማካሄድና ከዚህ የተጨመቁ ጽሁፎችን በኘሮሲዲንግ መልክ በዓመት አንዴ ማውጣት ነበር። ሁለተኛው ጆርናል ኦፍ ኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚል የምርምር መጽሄት በዓመት ሁለቴ ማውጣት ነው።

በኢኮኖሚስቶች ዙሪያ የሚካሄዱ ውይይቶች፣ ጥናቶችና ምርምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ ኅብረተሰቡን በጥያቄዎቹ ላይ የበለጠ ንቅቶ እንዲሳተፍ ማድረግም ነው። ስለዚህ ውይይቱ እርስ በርሳችን ብቻ መሆን የለበትም ከሚል ተነስተን ሦስት ኘሮጀክቶች አዘጋጀን።

አንደኛው፣ በየሁለት ወሩ የሚካሄድ የክብ ጠረጴዛ ውይይት ነው። ከዚህ ቀደም በኢኮኖሚ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ በፖሊሲ አውጭዎችና በሌላው የኅብረተሰብ ክፍል መሃል ይህ ነው የሚባል ውይይት

ተካሂዶ አያውቅም ነበር። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዲያድግ ካስፈለገ የመንግስት ባለሙያዎች፣ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች፣ የግል ባለሃብቶች፣ በአንድ ላይ መምከር አለባቸው።

ሁለተኛው፣ የክብ ጠረጴዛ ውይይት ሁሉንም ሊያሳትፍ ስለማይችል ውይይቱ ወደ ኅብረተሰቡ ዘልቆ እንዲገባ በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚታተም "ልሣን - ኢኮኖሚክስ" የሚል መጽሄት ማውጣ[illegible] ጀመርን። ዋና ዓላማው ውይይቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች ባሻገር ሰፋ ያለ የኅብረተሰብ ክፍል እንዲወያይበት ነው።

ሦስተኛው፣ ከሪፖርቱ ጋር በተዘጋጀው ፕሮጀክታችን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ ውይይት ስንገመግም፣ /በመሠረቱ ውይይት የሚባል ነገር የለም/ አሃዝ ጨብጦ መሠረታዊ እውነታዎች ላይ ውይይት አይደረግም። አሃዙን የሚያወጣው መንግሥት ነው። ያንን በጥንቃቄ የሚያየውና ለኅብረተሰቡ የሚያቀርበው የለም። ይኼ ትክክል ነው አይደለም የሚል ውይይት ማካሄድ አይቻልም። ስለዚህ በዘፈቀደ ዝም ብሎ ነበር ውይይቱ የሚካሄደው። እኛ ደግሞ፣ በየዓመቱ ከመንግሥት ውጪ ያለን ባለሙያዎች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንዴት እየሄደ ነው የሚል ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለብን።

ይኼ ሪፖርት ለመንግስት፣ ለፖርላማ ሰዎች መሰጠት፣ ለሕዝቡም መከፋፈል አለበት። ሕዝቡ ይኼንን አይቶ መንግሥት ከሚለው ጋር እያነጻጸረ፣ እውነትም ኢኮኖሚያችን እንደዚህ እየሄደ ነው ወይ? እነዚህ ችግሮች የተነሱት ለምንድነው? መፍትሄውስ ምንድነው? በሚል ገንቢና ቀና የሆነ ውይይት ማድረግ አለበት ከሚል ነው ይኼን ፕሮጀክት የጀመርነው።

የመጀመሪያው ሪፖርት እንደ ስርቬይ ሆኖ ይቅረብ አልን። ከደርግ የመጨረሻው አስር ዓመትና የኢሕአዴግ ዳታ እስከሚገኝበት ያለውን እንውሰድና በአጠቃላይ የሃያ ዓመቱን እንገምግመው አልን። አንደኛ የኢኮኖሚው መዋቅርና የተለያዩ ሴክተሮች ምን እንደሚመስሉ እናቅርብና ከሁለተኛው ሪፖርት ጀምሮ የምንወያየው ግን ባለፈው ካቆምንበት ዳታ እንዲሆን ወሰንን። በዚህም መሠረት ነው ይኼ ባለ 430 ገጽ ሪፖርት የተዘጋጀው። አሁን ለጊዜው በእንግሊዘኛ ነው የወጣው፤ ወደ አማርኛ እየተተረጎመ ነው። በአማርኛ የምናወጣበት ምክንያት የሀገራችን ሰው በትክክል አይቶ፣ የችግሮቹን ምንጮች ለይቶ፣ ከዚህ ችግራችን ለመውጣት ምን እናድርግ ወደሚል ገንቢ ውይይት እንዲገባ ነው።

*__ዜጋ__:- ሪፖርቱ ምን ዓይነት ግኝቶች ነበሩት?*

__ዶ/ር ብርሃኑ__:- እንግዲህ እኛ ራሳችን ስንሰራ ከጠበቅነው ውጪ ብዙ ነገሮችን ነው ያየነው። እንዲህ ዓይነት ምርምርም አስገራሚና አስደሳችም የሚሆነው እዚህ ላይ ነው። በመጀመሪያ እስኪ ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ጋር በማስተያየት የት ላይ እንዳለች እናስቀምጣት አልንና ትንሽ የቤት ሥራ ሰራን።

እንዲህ ዓይነት መረጃዎችን ማወቅ የሚቻለው ዓለም አቀፍ ዳታዎችን በመጠቀም ነው። በዚያም መሠረት የዓለም ባንክን፣ የUNDP ዳታዎችን አየን። በሁለት መስፈርት ነው ያወዳደርነው። አንደኛው በሂዩማን ዴቨሎፕመንት ሪፖርቱ ላይ ባለው፣ 'ሂዩማን ኢንዴክስ' መሠረት የሚል ነው። ሁለተኛው ዝም ብሎ በዓመታዊው በነፍስ ወከፍ ገቢው ሂሳብ ነው።

*__ዜጋ__:- በእነዚህ ሪፖርቶች እኛ የት ላይ ነን?*

__ዶ/ር ብርሃኑ__:- የUNDP የመጨረሻው ሪፖርት ከ174 አገሮች ውስጥ 172ኛ ያደርገናል። የዓለም ባንክ ደግሞ በነፍስ ወከፍ ገቢ የመጨረሻው ማነጻጸሪያ መረጃ ላይ ከ210 ውስጥ 210ኛ ያደርገናል። ይህ ለእኛ አስፈላጊ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለኢኮኖሚው ሲያወራ ድህነት እንዳለ ቢያውቅም የተሳሳተ ግንዛቤ ያለው ይመስለናል። "ማርና ቅቤ የሚፈስባት ሀብታም አገር" ስላለመሆኗ በግልፅ አስቀመጥን፣ በትክክል የመጨረሻዋ ወዳቂ ሀገር ናት የሚለውን ያሳያልና እርሱን መጠቀም ፈለግን። ዓላማውም ኅብረተሰቡ ከገባበት ከዚህ ሰፊ እንቅልፍ እንዲነቃ ለማድረግ ነውና ትንሽ የሚመታ [illegible] ስለነበርና ያንን ዳታ ተጠቀምን።

ሁለተኛ ደግሞ እኛን ከሌሎች ደሀ ሀገሮች ጋር ለማወዳደር ሞከርን። ቀላል ስሌት ነው የተጠቀምነው። አሁን ያለው የነፍስ ወከፍ ገቢው ምን ያህል ነው? የአፍሪካ አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ ምንድነው? አልንና በዚያ አንጻር ኢትዮጵያ እነርሱ ያሉበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድባታል ብለን ጠየቅን። በጣም የሚያስደነግጠው አንዱ ግኝት ይኼ ነበር። ይህንን ለማስላት አንዳንድ ግምቶች መውሰድ ነበረብን። ከነዚህም አንዱ በትልቁ ብናድግ በስንት ነው? ብለን ወሰድን። በ10 ወይም በ7 ፐርሰንት ኢኮኖሚያችን /የነፍስ ወከፍ ገቢያችን/ ቢያድግ በ3% የሕዝብ ቁጥር ማደጉ ከግምት ገብቶ አፍሪካ ላይ ለመድረስ ቢያንስ 42 ዓመት ያስፈልገናል። ወደሌላው ደሀ ሀገር ላይ ለመድረስ 43 ና 44 ዓመት የሚወስድ፣ በጣም የሚያስደነግጥ ዓይነት አሀዝ አገኘን።

በዝርዝር በየሴክተሩ ስንገባ ደግሞ አንዳንድ ችግሮች ማየት ጀመርን። ጥቂቱን ለመንካት አንዱ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው። አጠቃላይ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በምንድነው ያደገው? አልን። የኢትዮጵያ መንግሥት የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚውን ለማጠናከር ብሎ እርሻ መር ኢኮኖሚ ባለፉት ስድስትና ሰባት ዓመታት እየተጠቀመ ነው። ይኼ ነገር ምን ያህል ውጤት እንዳመጣ ለማየት ዘርዘር አድርገን አየነው።

በአጠቃላይ የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ አማካይ ዕድገት ስናየው በጣም ዝቅተኛ፣ ከደርግም የመጨረሻ 10 ዓመት ጋር ስናስተያየው ያነሰ ነው። በደርግ የመጨረሻ ዓመታት 2 ከመቶ ነበር የሚያድገው። እስከ 1998 ዓ.ም. /እ.ኤ.አ/ ያለው ዕድገት ደግሞ በ1.6 እና በ1.7 ከመቶ ነው።

የሁላችንም ግምት የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ጥሩ እያደገ ነው የሚል ነበር። ምክንያቱም ፖሊሲው በአንፃራዊነት ጥሩ ነው፣ የማዳበሪያ ስርጭትም አለ ይባላል። ከዚያ ጠለቅ ብለን ግን ስናየው የተለየ ሆነ። ለዚህ ችግር ምክንያቱ ያጋጠሙት ሦስት የድርቅ ዓመታት ነበሩ። በነዚያ ዓመታት እድገቱ ከዜሮ በታች ነው። ጥሩ በምንሰራና ጥሩ ዝናም ባገኘን ጊዜ ደግሞ ከበፊቱ በበለጠ በጣም እናድጋለን።

*__ዜጋ__:- በዚህ አሀዝና መረጃ ላይ ከመንግሥት ሰዎች ጋር ምን ዓይነት ልዩነት ነበር?*

__ዶ/ር ብርሃኑ__:- ትልቅ ክርክር የነበረው 1990-91ን እንደ መነሻ ዓመት ለምን ትወስዳላችሁ የሚል ነው። ያ ወቅት በፖለቲካው መጥፎ ጊዜ ነው፤ ምክንያቱም የፖለቲካ አለመረጋጋት የነበረበት ዘመን ነው፤ እሱን መውሰድ የለባችሁም የሚል ነበር። በመሠረቱ ጥሩ ክስና የውይይት መሠረት ነው። በእኛ በኩል ደግሞ በፖለቲካው ሰበብ በጣም ዝቅተኛ ምርት የተገኘበት ዘመን ነው። እርሱን ትተን የ1991-92 ስንወስድ ደግሞ የናረ ነው። 12 ከመቶ በላይ ነበር ያደገው። ይኼ ዕድገት የተገኘው ፖሊሲው ሠርቶ፣ እድገት ተገኝቶ ሳይሆን በችግሩ ጊዜ በጣም ዝቅ ስላለ፣ ለማንሰራራት ሲባል የተዘጉት ፋብሪካዎች ስለተከፈቱ ከውድቀቱ በመነፃፀር የታዬ ዕድገት ነው። የእኛ ክርክር እርሱንም ቢሆን መውሰድ የለብንም የሚል ነው።

ይኼንንም ትተን 1992-93 ላይ ከጀመርን እኛ እንዳልነው ይወርዳል። ስለዚህ ለሁሉም ተገቢ የሚሆነው ከ1990-91 መጀመሩ

ነው። እርሱ ብቻ አይደለም፤ ከ1991-92 እንኳ እነርሱ ጥሩ ጊዜ በሚሉት ቢጀመር፣ ማለትም በመንግሥት ፖሊሲ ሳይሆን በራሱ ባገገመበት ጊዜ ቢታይ እንኳ፣ የእርሻው ዕድገት 2.26 በመቶ ነው። ከደርግ ጊዜ ትንሽ ይሻላል፣ ግን ያን ያህል አይደለም። ይኼ ለኅብረተሰቡ ግልፅ መሆን አለበት።

በእኛ እምነት የኢትዮጵያ የእርሻ ችግር ምክንያቱ ዝም ብሎ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ችግር አይደለም። መዋቅራዊ ነው። ስለዚህ በየዘርፉ የሚገጥሙን የፖሊሲ ፈተናዎች /ሳንካዎች/ ምንድናቸው ብለን በአንድ ምዕራፍ በዝርዝር ተወያየንባቸው። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁን ካለበት የገበሬ ኢኮኖሚ መውጣት መቻል አለበት የሚለው ወሳኝ እንደሆነ ተረዳን። በረጅም ጊዜ ዓላማ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከመሠረቱ መቀየር አለበት። 85 ከመቶ የሚሆነው ኅብረተሰብ ተፈጥሮአዊ እርሻ ላይ ሆኖ ዕድገት የለም።

*ዜጋ፡- መፍትሄው ምንድነው?*

ዶ/ር ብርሃኑ፡- ኢንዱስትሪውን የምናሳድግበትና በኢንዱስትሪው ላይ ያተኮረ ፖሊሲ የግድ ያስፈልገናል። ይኼ ደግሞ ኅብረተሰቡን ከእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ስለሚያነሳው፡-

አንደኛ፣ በእርሻው ላይ ያለው ምርታማነት እየጨመረ ይሄዳል። በአማካይ የመሬት መጠን እያደገ በሚሄድበት ጊዜ ምርታማነትም ይጨምራል። ሁለተኛ፣ ተጨማሪ ዋጋ ያለው፣ ተጨማሪ እድገት ሊያመጣ የሚችለው ኢንዱስትሪው ነው። እንደ ስልት ወደዚያ ነው መሄድ ያለብን። አሁን ደግሞ ያ ስልት የለም። በመንግስት ደረጃ እርሻ መር የሆነው ፖሊሲ የሚለው፣ እርሻውን ስታሳድገው ኢንዱስትሪውም አብሮ ማደግ ይችላል ነው እንጂ ኢንዱስትሪውን እናሳድግ የሚል (Converted) ስትራቴጂ የለም። በኢንዱስትሪያል ፖሊሲው ኢትዮጵያ ያላት የተሻለ አማራጭ በየት በየት በኩል እንደሆነ ማየት ነው። ዋናው ኢንዱስትሪያላዜሽን ነው።

ኢንዱስትሪያል ፖሊሲ ስላለ ደግሞ ሁሉንም ነገር ልናመርት አንችልም። አጥንተን፣ በተጠኑ ምርቶች ላይ ከዓለም ተወዳዳሪ የሚያደርግ ራዕይ ያለው የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በመቀየስ መንግሥትና ባለሀብቱ ተባብሮ እነዚያን ለማሳደግ እንዲረባረብ ማድረግ ነው። ለምሳሌ፣ የውጭ ንግድ ፖሊሲያችን ዝም ብሎ ነፃ ገበያ እናድርግ በሚል ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና ሳይሆን፣ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ጥረትን ሊያሳድግ በሚችል መልኩ መቀረጽ አለበት። ኢንዱስትሪዎችን ስንፈጥር እነኝህ ኢንዱስትሪዎች ከሌላው ዓለም ጋር ተወዳዳሪ እስኪሆኑ ድረስ ከውጭው ውድድር መጠበቅ አለባቸው። በተወሰነ ደረጃ የውጭ ንግድ ፖሊሲው በቀረጥ፣ ድጎማ በማድረግ ከለላ መስጠት አለበት። በመሆኑም የውጭ ንግድ ፖሊሲያችን ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር ይያያዛል።

*ዜጋ፡- ያቀረባችሁትን አማራጭ መንግሥት ተቀብላችሁ?*

ዶ/ር ብርሃኑ፡- መጽሐፉ በመንግሥት አካባቢ በተወሰነ ደረጃ ተሰራጭቷል። ያዩትም ይመስለኛል። ለነገሩ ይኼ እኮ ከመንግሥት ጋርም የሚያጣላ አይመስለኝም። እነኚህን ጥያቄዎች መንግሥትም በተወሰነ ደረጃ እያሰበባቸው ይመስለኛል።

ከአንዳንድ ቦታ እንደምሰማው፣ ለምሳሌ ያስፈልጋል የምንለው ኢንዱስትሪያሊዜሽን በአዲሱ መርሀ ግብር ተካቷል የሚል ነው። በመሆኑም ሁላችንም ብንወያይ የምናስበው ለአንድ ሀገር እድገት ስለሆነ የሚያለያዩን ነጥቦች ያን ያህል አይደሉም። ችግሩ ያለው ቁጭ ብሎ አለመወያየትና የእኔ ብቻ ነው ትክክል ማለት ላይ ነው። እንደማስበው ከሆነ ባለፈው በተባበሩት መንግሥታት የስብሰባ አዳራም ሆነ እኛም የምናደርጋቸው ውይይቶች ይኼን ክፍተት ለማቀራረብ ነው።

በመሠረቱ ይኼ እኮ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ምርጫ የማጣት ጉዳይ ነው። ከዚህ ሌላ ምንም ምርጫ የለንም። ይልቅስ ኅብረተሰቡን አስተባብሮ ወደዚያ እንዲያስብ ማድረግ ነው። ሁላችንም በአንድ ላይ ልናደርገው የሚገባ ይመስለኛል። ምናልባት በመሬት ጥያቄ ላይ ትንሽ የሚያከራክሩ ነገሮች ይኖራሉ። እኛ መሬት የግል ይሁን የመንግሥት ይሁን፣ የሚል ውይይት ውስጥም አልገባንም። ለእርሻው ክፍል ማነቆ የሆነው በገበሬው ዘንድ የመሬት ባለቤትነት ስሜት አለመስማት መሆኑን ነው የተናገርነው።

*ዜጋ፡- ብዙውን ጊዜ ስለዕድገት ሲናገሩ የሕዝቡን ተስፋ መቁረጥ ይናገራሉ። ምክንያትም ምንድነው?*

ዶ/ር ብርሃኑ፡- ይኼን ጥያቄ ከዚህ በፊትም ሁለት ሦስት ጊዜ አንስቼዋለሁ። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ድህነት ፍጹም ለከት የሌለው ነው። ወገብ የሚሰብር፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ ድህነት ከመሆኑ የተነሣ አብዛኛው ሕዝባችን በአስተሳሰብ ደረጃም ኑሮዬን የማሻሻልና የማሳደግ መብቱ እኔ ላይ ነው የሚል ስሜቱን ሙሉ በሙሉ አሳጥቶታል። ላለበት የኑሮ ችግር መፍትሄ የሚፈልገው ከራሱ ውጭ ነው። ቢርበን ቢጠማን የውጭ ሰዎችን እጅ ነው የምናየው።

ደሀው ከድህነት ለመውጣት የሚያስበው ሌላው ሰው ሲረዳው ወይም ገንዘብ ሲሰጠው፣ ወይም ከመንግሥት ሲያገኝ እንጂ በራሴ አንድ ነገር አደርጋለሁ የሚል በራስ የመተማመን መንፈሱ አፈር እየበላ ነው፤ አሊያም እድሌ ያመጣውና ምንም ላደርገው የማልችለው ነው ብሎ ለእግዚአብሄር ሰጥቶ ተቀምጧል።

እድገት ማለት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የኅብረተሰብ ለውጥ ማለት ነው። ያ ለውጥ ደግሞ በአብዛኛው ካደጉ ሀገሮች የምናየው ኑሮን ለማሸነፍ ያለው ዕድል በግለሰቡና ብሎም በማኅበረሰቡ ላይ ያረፈ ነው። "ህይወትን የሚቀጥፍ በሽታን ርምጃ በመውሰድ እናቆመዋለን" ብሎ ነው የሚያምነው እንጂ፣ ለእግዚአብሄር እንተውለት ብሎ አይተውም። ከባህላዊ አስተሳሰብ ወደ ዘመናዊ መምጣት ማለት ይህ ነው። እኛ ይኼን እያጣን ነው። በራስ መተማመን እስከሌለ ድረስ የትም አንደርስም። ተከታታይ የሆነ ድህነት ያመጣውን ቅስም የመስበር ሁኔታ በማስወገድ የኅብረተሰቡን በራስ የመተማመን ችሎታ፣ ራሴ ኑሮዬን አሸንፋለሁ የሚለውን ተስፋ ማጎናፀፍ አለብን።

ችግሩ የደሀው ብቻ አይደለም። መንግሥት እኛ የፈጠርነው፣ እኛ ያቋቋምነው ተቋም መሆኑ ቀርቶ ልክ ከበላያችን በእግዝአብሄር የተቀመጠ አድርገን እናየዋለን። ሀብታሞች ከመንግሥት ጋር ካልተሞዳሞዱ፣ ንብረት የሚሰሩ አይመስላቸውም። የተማረው ሰው ከመንግሥት ጋር ካልሰራ ኑሮው የሚያቆም ነው የሚመስለው። ይኼ የግለሰብን ተነሳሽነት የሚያሳጣ አስተሳሰብ ነው። ወደዚያው ውስጥ እየገባን ነውና ከዚያ እንውጣ ነው፤

*ዜጋ፡- ከዚህ ጋር በተያያዘ በልሂቃኑ ላይም በተደጋጋሚ የሚያቀርቡት ወቀሳ አለ? ይህ ከምን የመጣ ነው?*

ዶ/ር ብርሃኑ፡- ልሂቅ (Elite) በሚባለው ላይ በእርግጥም ብዙ ጊዜ ተናግሬያለሁ። እንዳያውም ትንሽ ላጋነውና አንዳንድ ጊዜ ሳስበው የኢትዮጵያ ሕዝብ አይነተኛ ችግሩ ከዚህ የኅብረተሰብ ክፍል የመጣው ነው የሚል ድምዳሜ ላይ እየደረስኩ ነኝ። ከደሀው ይልቅ እነርሱ ናቸው ዋናዎቹ በሽተኞች። ሁለት ምክንያት አለኝ። አንደኛ፣ በተለይ ትንሽ ተማርኩ የሚለው ክፍል በፍርሀትና ቅድም

## "...ሻዕቢያ ሊያንሰራራ...

ከገጽ 11 የዞረ

ይገዛናል፣ የሚል ሀሳብ ነበረው። ግን አሁን የምርጫውን ውጤት ስንመለከት በተለይም በአዲስ አበባ አስገራሚ የሆነ ተስፋ ሰጭ የተቃዋሚዎችን አሸናፊነት ነው ያየነው። ከምናውቃቸው ውስጥ በወረዳ 18 በኢሕአዴግ የቀረቡት አቶ ተፈራ ዋልዋ ተሸነፉ። ያ የሚያሳየው ለካ በድምፅ መንግሥት መቀየር ይቻላል፣ የሚለውን ነው። ዛሬ በዚህ ሁኔታ አቶ ተፈራ ወደቁ፤ ኅብረተሰቡ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተካፍሎ ቢሆን የተለየ ይሆን ነበር። ከአምስት ዓመት በኋላ ተቃዋሚው ተከፋፍሎ ድምፁን ሳይበትን አንድ ወጥ የሆነ የኢሕአዴግ አማራጭ ሆኖ ቢቀርብ፣ ቅድም እንዳልኩት ልሂቁ በየመሸታ ቤቱ ማውራቱን ትቶ ሂደቱ ውስጥ ቢገባ፣ በእርግጥም መሠረታዊ የሆነ የፖለቲካ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።

መንግሥት እንኳ ባንለውጥ፣ መንግሥት ከአሁን በኋላ የኅብረተሰቡን ድምፅ አያጣጥልም። በአንጻሩ ኅብረተሰቡ የሚለውን መስማት ግዴታው ይሆናል። በሥልጣን ከባለገና የሚጠበቀበትን ካላደረገ ደግሞ ሊቀይረው እንደሚችል ያሳያል። ይሄም እኮ ነው የለውጥ ሂደት ማለት። በእርግጥ ከዚህ ተገቢ የሆነውን ትምህርት መውሰድ ከቻልን በጠቅላላው ፖለቲካችንን ነው የሚቀይረው። በዚህ ምርጫ ምንም ማጭበርበር አልተካሄደም ማለት አይደለም። ግን በዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እዚህ መድረስ መቻሉ ነው ሊያስተደስተን የሚገባው።

***ዜጋ፡-*** *እነ አቶ ዓሊ አብዶ ወደቁ ከተባለ በኋላ እንደገና ማለፋቸው ተነገረ። ይኼ ሁኔታ ባጫረው ተስፋ ላይ ተፅዕኖ አይኖረውም?*

**ዶ/ር ብርሃኑ፡-** ያለን መረጃ በሙሉ የሚያመለክተው አቶ ዓሊ አብዶ 7ኛ መውጣታቸውን ነበር። 7ኛ ወጥተው በሆነ ማጭበርበር እንዲያልፉ አድርገው ከሆነ በዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ላይ ጥቁር ነጥብ የሚጥል ነው። ይኼን ለማረጋገጥ መጀመሪያ ምርጫው በምን ሁኔታ ነበር የተቆጠረው? ታዛቢዎች በሙሉ ነበሩ ወይ? በዝርዝር ተመዝግቧል ወይ? የሚሉትን ማየት ነው። ተደርጎ ከሆነ የምርጫ ቦርድ በሚባለውና ምርጫ አስፈጻሚው ላይ ያለንን እምነት የሚያሳጣን ነው። ነፃና ገለልተኛ በሆነ መልክ መጣራትም አለበት። እነዚህ ትናንሽ ነገሮች ናቸው ሕዝቡን በምርጫው ላይ እምነት የሚያሳጡት። መንግሥትም ይህንን በጥንቃቄ ሊያየው የሚገባ ይመስለኛል።

በመጀመሪያ ሰባተኛ ናቸው የተባለው ውሸት ከሆነም ልክ አይደለም። ያልሆነን ነገር እንደሆነ ተደርጎ ወድቀዋል ብሎ አስወርቶ በኋላ እንዲህ ዓይነት መጥፎ ስሜት እንዲፈጠር ማድረግ ጥሩ አይሆንም።

***ዜጋ፡-*** *በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ላይ ባለሙያዎችና የሙያ ማኅበራት በሀገራችው ውስጥ ምን ሚና ሊኖራቸው ይገባል?*

**ዶ/ር ብርሃኑ፡-** የሙያ ማኅበራት የሚኖቸራው በጣም ሰፊ ሚና ነው። ዴሞክራሲ በእውነት ፖለቲከኞች ከላይ ሆነው የሚሰጡን አይደለም። የኅብረተሰብ እንቅስቃሴ ውጤት ነው።

ለምሳሌ፣ የህክምና ማኅበር ሕክምናን፣ ጤናን በሚመለከት ሰፋ ያለ ዕውቀት ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ነው። ስለሆነም ህክምናን በተመለከተ ፖሊሲ ሲወጣ፣ ርምጃ ሲወሰድ ዝም ብሎ ሊቀመጥ አይገባም። መንግሥት እንዲያማክረው የግድ መገፋፋት አለበት፤ ካላማከረው ደግሞ በዚያ ጥያቄ ዙሪያ ኅብረተሰቡን የማስተማር ኃላፊነት አለበት። ግን በእኛ ሀገር ፍርሃቱ ስላልለቀቃቸው መሠረታዊ የሆነ ሙያቸውን የሚመለከት የኅብረተሰብ ጉዳይ ሲመጣ ምንም ነገር አይሉም።

የኤድስና የወባ ችግር እንዲህ ሀገሪቱን ሲያናውጥ፣ የሀኪሞች ማኅበር እንዲህ ቢደረግ ይሻላል ብሎ ለኅብረተሰቡ ግልፅ የሆነ አንድ ነገር ሲያወጣ አላየንም። ሰብአዊ መብቶች ሲነፈጉ፣ ፍ/ቤቶች ሕዝቡን በቀጠሮ ሲያጉላሉ የጠበቆቹ ማኅበር አንድም ቀን ምንም ሲል ሰምተን አናውቅም። እነኝህ እኮ ናቸው ታዲያ መንግሥትን የሚቆጣጠሩት። መንግሥት ኅብረተሰቡን የማይጠቅም ሕግ ሲያወጣ ይሄ እኮ ልክ አይደለም ብለው ከሙያቸው ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ለፖለቲከኞች አሳልፈው የሚሰጡበት ምክንያት የለም። ሽንጣቸውን ገትረው መንግሥት እንዲሰማቸው ማድረግ አለባቸው።

***ዜጋ፡-*** *በቢሮክራሲው ውስጥ ስለ የፖለቲካ ታማኞች ምን አስተያየት አለዎት?*

**ዶ/ር ብርሃኑ፡-** ከዚህ ቀደም ሁለት ሦስት ጊዜ አንስቼዋለሁ። መንግሥትም በተደጋጋሚ ያነሳዋል። እንደሚታወሰው በውይይት ጊዜ የመሬት ፖሊሲ፣ የሊዝ ጉዳይ፣ ወዘተ ሲነሣ መንግሥት አፈጻጸሙ እንጂ ፖሊሲው ችግር የለበትም ነው የሚለው። ያ ማለት ፖሊሲው ጥሩ ነው ይባልና ታች ማነቆ ይፈጠራል ነው። እንግዲህ መንግሥት የሚሾማቸው ብቃት የሌላቸውን፣ ነገር ግን የመንግሥት ታማኝነታቸውን ብቻ እያየ ነው ማለት ነው። ሌላው ፖሊሲው በጣም የተወሳሰበና የሚከብድ ነው ከተባለ ደግሞ ፖሊሲው መጥፎ ነው ማለት ነው።


በየቦታው የሚቀመጡ ሰዎች ፖሊሲ የመተርጎም ዕውቀቱና ልምዱ ሳይኖራቸው የፖለቲካ ታማኝነት ብቻ ታይቶ ነው። ዕውቀቱ ያላቸው ግን ቦታውን አላገኙም። ሥራና ሠራተኛ አልተገናኙም። መንግሥት የፖለቲካውንና የአስተዳደሩን ሥራ በደንብ መለየት አለበት። ሙያውን በባለሙያ ማስያዝ፣ በተለይም አስተዳደሩን። ፖለቲከኞች ፖለቲካውን ይምሩት፤ አፈጻጸም ላይ ግን ባለሙያዎች ይስሩት። ሙያን ከፖለቲካ ታማኝነት ብንለየው ትንሽ በአፈጻጸም ላይ ያሉንን ችግሮች ልንቀርፍ እንችላለን።

***ዜጋ፡-*** *ስለጦርነቱ ያለዎት አስተያየት ምንድነው? መፍትሄ ይኖረዋል?*

**ዶ/ር ብርሃኑ፡-** መፍትሄ ይኖረዋል፣ አይኖረውም? የሚለው ላይ በኋላ እንመጣለን። ይህን ጥያቄ ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት በማኅበራችን በኩል አንስተነው ነበር። ከኢኮኖሚው አኳያ ካየነው ጦርነት በምንም መልኩ መጥፎ ነው። ምክንያቱም ሠላምና መረጋጋት በሌለባቸው አካባቢዎች የኢኮኖሚ እድገት ሊኖር አይችልም። ጦርነት ብዙ ውድ የሆኑ ወጪዎችን የሚያስወጣ ነው:- ገንዘብ፣ የሰው ህይወት፣ ወዘተ...

በተቻለ መጠን ጦርነትን፣ ውስጣዊ አለመረጋጋትን ማስወገድ ግዴታ ነው። ስለዴሞክራሲ የምናወራው ለዚህ ነው። ሕዝቡ የሚመራውን ከመረጠ በሀገር ውስጥ የተረጋጋ ሁኔታ ይኖራል። የተረጋጋ ሁኔታ ሲፈጠር የኢኮኖሚ ዕድገት ይመጣል። ከኤርትራ ያየነው ነገር ሰላም አንድ ወገን ስለፈለገው ብቻ የሚገኝ አለመሆኑን ነው። ሠላም በተወሰነ ደረጃ በአካባቢ ነገሮችም ተቀባይነትን ሲያገኝ ነው ሠላም የሚመጣው። ተንኳሽነት ባለበት ሊመጣ አይችልም።

የኤርትራ ወረራ ከተጀመረ አንስቶ ፍጹም ግራ የገባኝ ኤርትራ ለምን እንደወረረችን ነው። በተለያዩ አጋጣሚዎች ብዙ የውጭ ዲፕሎማቶችን ሳገኝ ወራሪውን ሀገር ውጣ ለማለት ምንድነው ችግሩ? የሚለው በጣም ግራ ስለሚገባኝ፣ ምናልባት እኛ የማናውቀው፣ እነርሱ የሚያውቁት በኢትዮጵያ በኩል የተወሰደ የመተንኮስ ርምጃ ይኖር ይሆን ወይ ብዬ ጠይቄ ነበር። ብዙ ጊዜ



ያገኘሁት መልስ "የለም" ነው። እዚያ ላይ ግልፅ ነው። በግንቦት ወር ላይ ኤርትራ ናት የወረረችን።

ይኼ የሚያሳየው ሳይፈለግ ጦርነቱ መምጣቱን ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ኢኮኖሚውን በሚመለከት እንዴት ነው መወጣት የሚችለው? በሚለው ላይ ውይይት ስናደርግ የተናገርኩት አሉ፡ ወጪው የሚበዛው ጦርነቱ ከተራዘመ ነው። በዚያን ወቅትም እንዴት እንወጣዋለን? ለሚለው ስድስት አማራጮችን ለማቅረብ ሞክሬ ነበር። በጣም መጥፎ ያልኩት ጦርነቱ ውስጥ ገብተን ኤርትራ ብታሸንፈን ነበር። እርሱ በጣም መጥፎ ነው። ከዚያ ቀጥሎ በኤርትራ የሰላም ፍላጎት መንገድ ውስጥ ብንገባ በጣም ከፍተኛ ወጪ ነው ያለው። ሌላው ወጪ የሚያስወጣን ዝም ብለን የምንቀመጠው ነገር ነበር። በዚያን ጊዜ ከተቻለ ይኼን ጦርነት በቶሎ የምናቆምበት መንገድ ቢመቻች ብለናል። ከዚያ በኋላ አንድ ዓመት ተኩል ቆየን። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሦስት ነገሮች አየን።

<u>አንደኛው፤</u> የውጭ ኃይሎች ሠላም ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ ከንቱ እንደሆነ ተመለከትን። በተለይም ለእነርሱ ጥቅም ሆኖ ካገኙት ኤርትራን ለዘላለም ሊያባብሉ እንደሚችሉ አወቅን።

<u>ሁለተኛው፤</u> ያለሰላም ያለጦርነት መቀመጥ ምን ያህል ኢኮኖሚያችንን እንደጎዳው አይተናል። የውጭ ምንዛሬያችን በመጎዳቱ በንግዱ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። አልተዋጋንም እንጂ ወጪዎቹ አልቀሩም ነበር። በእርግጥ ባለመዋጋታችን ሰው አልሞተ ይሆናል እንጂ በመሣሪያ ግዢውም ሆነ በአጠቃላይ ከሠራዊቱ ወጪ አንጻር ወጪዎች አልቀሩም። የውጭ ምንዛሬያችን ከማሽቆልቆሉ የተነሣ 100% ሌተር ኦፍ ክሬዲት አስቀምጡ ተብሎ የውጭ ንግዳችን ተጎድቷል።

<u>ሦስተኛው፤</u> የውጭ ባለሀብቶች ጦርነት ላይ ስላለን ቱሪስቶችም ስለሚፈሩ አልመጡም፤ ይህ ሁሉ ወጪ ነው። ይኼ ዝም ብሎ መቀመጡ ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም። የኢትዮጵያ መንግሥትም ወጪዎቹን ለመጠበቅ ኢኮኖሚውን እየጎዳሁ መቀመጡ ይብቃኛል ብሎ ነው ይኼን ጦርነት የከፈተው።

በእኔ እምነት ይኼ ጦርነት ሙሉ በሙሉ መደገፍ ያለበት ርምጃ ነበር። ጦርነቱ ፍትሀዊ ነው። እንደ ዜግነቴ /እዚህ ላይ አፅንኦት ልሰጥ የምፈልገው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገር ጉዳይ ላይ ንቁነቱን ነው።/ ሀገር በምንም መልኩ ጦርነት ውስጥ ስትገባ የሚዋጉ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችንና ልጆቻችን በመሆናቸው መደገፍ ትክክለኛ ርምጃ ነው። አሁን እንደሚታየው በለስ እየቀናን፣ ጥሩ እየተራመድን ድል በድል ሆነናል። የጠበቅነውን ያህል ቀርቶ ግማሽ ያህል መቋቋምን አላየንም። የኢትዮጵያ ጦር በእውነት የማንም ጉልበተኛ እንደፈለገው የማያደርገው መሆኑን ያሳየበት ነው።

ከዚህ በኋላ የዚህ ጦርነት የመጨረሻ ግብና ስትራቴጂ ምንድነው? በሚለው ላይ የተወያየንበትና መንግሥትም ግልፅ ያደረገልን ነገር የለም። ዛላአንበሳን ይዘን፣ የተጠናከረ ጦር አስቀምጠን እንደገና አስር ዓመት ቆይቶ እንዲወረን ነው? ወይንስ አንድ ዘላቂ መፍትሄ እንፈልጋለን? እኔ በፊትም ይኼ ጦርነት የተከፈለው መስዋዕት ተከፍሎ ተመልሰን የማንገባበት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለብን የሚል ጠንካራ እምነት አለኝ። ለዚህ ደግሞ እንዱ የሻዕቢያ ጦር ዳግም ሊያንሰራራ በማይችልበት መልኩ መመታት አለበት የሚል ነው።

ሁለተኛ እንደገና ለውይይት መከፈት ያለብን የዚህ የወደብ ጥያቄ ነው። እያደገ ያለ ስድሣ ሚሊዮን ሕዝብ ይዘን ያለ ባህር በር መቀመጥ እንችላለን ወይ? የሚለው በመንግሥት በኩል መታየት ያለበት ይመስለኛል። በምን መልክ የሚለውን እነዚሁ የመንግሥት ባለሟሎች የሚያዩት ነው። በአሁኑ ጊዜ በኢኮኖሚ ዕድገት የባህር በር የሌላቸውንና ያላቸውን ብናወዳድር የባህር በር የሌላቸው በአነስ ደረጃ መሆናቸው ታይቷል። ሁልጊዜ ዝቅተኛ የዕድገት ለውጥ የሚያስመዘግቡ የባህር በር የሌላቸው 20 የሚደርሱ የአፍሪካ ሀገሮች አሉ። ስለዚህም ለረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ጥቅማችን የባህር በር ጥያቄን ማንሳት የሚያስገድደን ይመስለኛል።

<u>ዜጋ</u>፡- *ስለባህር በር ሕጋዊ መድረኩስ የለንም?*

<u>ዶ/ር ብርሃኑ</u>፡- ሊኖር ይችላል። ሀገር ውስጥም ውጭም ባሉ በብዙ የህግ ባለሙያዎች አንድ የተጀመረ እንቅስቃሴ አለ። በሕግ የሚያስኬደን ጥያቄ ነው። እስካሁንም ይህንን የሚጎዳ ሥራ ሠርተን ከሆነ ይቅርታ ብለን መሄድ ነው ያለብን። የመንግሥት ኃላፊነት ከፖለቲካ ርዕዮት ወጥቶ የሀገር ጥቅም ምንድነው ብሎ ማስቀደም ነው።

አሜሪካና እንግሊዝ ዛሬ የዚህ ዓይነት ርምጃ የሚወስዱት ለፍትህ ወይም ለርዕዮተ ዓለም ሳይሆን ለጥቅም ብለው ነው። የሀገራችን ጥቅም ሳይጠበቅ ሀገር ሊኖር አይችልም። እንዲህ ሲባል የሚያመጣውን ዋጋ ራሱ ይክፈል ማለቴ ሳይሆን ጥቅሙን አመዛዝነን ለሀገራችን የሚበጀውን እናድርግ ነው።

<u>ዜጋ</u>፡- *የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን ማኅበር እስከመቼ ይመሩታል?*

<u>ዶ/ር ብርሃኑ</u>፡-ምናልባትም ይኼ በፕሬዝዳንትነቴ የማደርገው የመጨረሻው ቃለ ምልልስ ሳይሆን አይቀርም። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር በሕገ መንግሥቱ በግልፅ የተቀመጠ መስፈርት አለው። አንድ በፕሬዝዳንትነት የተመረጠ የድርጅቱ መሪ መወዳደር የሚችለው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። እያንዳንዱ ጊዜ ለሁለት ለሁለት ዓመት ነው። እኔ የሁለት ጊዜ ሥልጣኔን በዚህ በሰኔ ወር ላይ ጨርሻለሁ። ይህ፣ ከማኅበሩ እንደ አባልነቴ ከሚሰሩ ሥራዎች እገለላለሁ ማለት አይደለም። ግን በፕሬዝዳንትነት የምሰራበት የመጨረሻ ዓመት ነው። ሌሎች አዲስ መሪዎች ይተካሉ።■